Generated by Foxit PDF Creator © Foxit Software
http://www.foxitsoftware.com For evaluation only.

# በውዥንብር ዓለም-የትኛው ሃሳብ ነው ትክክል ?

## መግቢያ

እ.አ ከ 28.07-30.07.2011 ጀርመን አገር ኑርንበርግ ከተማ ላይ በተካሄደው የስፖርትና የባህል ፌስቲቫል ላይ በተገኘሁበትና ከብዙዎቹ እህቶቼና ወንድሞቼ ጋር ባደረጉት ጥልቅ ውይይት የተገነዘብኩት ነገር ፣ በአንድ በኩል የኢትዮጵያዊነት ስሜት ከምን ጊዜውም በበለጠ ያየለበት ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶችና ፣ ብዙ ከዚህም ከዚያም የሚሰነዘሩ በድህረ-ገጾች ላይ የሚወጡ ጽሁፎች ግራ መጋባትን ነው። ስለሆነም በትክክል የሚነሳው ጥያቄ ፣ ማንን እንመን ? ማንነው ትክክለኛው? ለምንስ ምሁሮች አንድ ላይ ሆናችሁ ተወያይታችሁ ለትግሉ የሚበጅ አንድ አቅጣጫ ለማሲያዝ አትሞክሩም? የሚል ነው። አንድ ሁሉንም የሚያስተሳስር ሃሳብ ግን ከሁሉም ግንባር ላይ ይነበባል። ይኸውም በወያኔ አገዛዝ ላይ ያለው ጥላቻ ነው። ከዚህ ቀደም ከፖለቲካ ጋር ምንም ግኑኝነት ያልነበራቸው እንኳ ሳይቀሩ የወያኔ አገዛዝ በአንዳች ዐይነት ነገር መወገድ እንዳለበትና ፣ ይህ እንደ ነቀርሳ የሚሰረስር አገዛዝ ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ የኢትዮጵያ ህልውና ተዳክሞና ፣ የአንድነታችን ምልክት የሆኑት ነገሮች ሁሉ ቀስ በቀስ ደብዛቸው በመጥፋት ኢትዮጵያ የምትባል አገር ለመኖር እንደማትችል ነው።

ከዚህ ጨለማ የሚመስል ነገር በመነሳት ብዙዎችን ያሳሰባቸውና እንቅልፍ የነሳቸው በየጊዜው እየተንጋጋ የሚወጣው የጽሁፍ ዐይነት ነው። አንዱ በአንድ ጊዜ ይነሳና ይህችን አገር ለማዳን የግዴታ ከዛሬው አገዛዝ ጋር መስራት አለብን በማለት ሰፊ ሀተታ ይሰጣል። ሰፊ ሀተታ ሲሰጥ ግን በምን ቅድመ-ሁኔታዎችና ለምንስ ዓላማ ከአገዛዙ ጋር ሁኖ አብሮ ያችን አገር „ለማዳን“ ይቻላል? የሚለውን ጥያቄ አያነሳም። በተጨማሪም ሰፊ ሀተታ በሚሰጥበት ጊዜ ሃያ ዐመት ያህል ባለማወቅ ሳይሆን ፣ በዕውቅና ከኔ በላይ አዋቂ የለም በማለት አገርን ካዳከመና ህዝብን ካደኸየ አገዛዝ ጋር እንዴት አድርጎ መስራት ይቻላል? የሚለውን ከባድ ጥያቄ በፍጹም አይነሳም። ስለዚህም ብዙዎችን ግራ የሚያጋባው እንደዚህ ዐይነቱ ሃሳብ ምሁራን ከሚባሉት መሰንዘሩ ነው። ለምንድነው እነዚህ ምሁራን ግራ የሚያጋቡን? የሚል ጥያቄ ከየቦታው እየተነሳ ነው። ከዚህ በተረፈ በዲሞክራሲና በሊበራሊዝም ፣ በቅርቡ ደግሞ በፖለቲካ ድርጅቶች መሀከል የአመራር ድክመትን አስመልክቶ ሁሉንም ሊያስማማና ሊያስተሳስረን የሚችለው „የኮንስቲቱሽናል ሞናርኪ“ ነው በሚል አንድ ሰፊ ሀተታ ቀርቧል። ሌሎችም ከኢንፎርሜሽን አልፎ እስከዚህም ድረስ ሁላችንን ሊያስተሳስርና አመለካከታችንና አስተሳሰባችንን ሊያሾል የማይችል ጽሁፍ ከዚህም ከዚያም እንደ አሸን ይፈልቃል። ኢንፎርሜሽኖችን የማሰራጨቱ ጉዳይ በጣም ጠቃሚ ቢሆንም ፣ ከትግል ስትራቴጂና አገርን ለመገንባት ከሚያስፈልገው ከትክክል ዕውቀት አንጻር ሲመረመር የሰዎችን አትኩሮ ይበታትነዋል። በተለይም በጥሩ ቋንቋ ተቀነባብሮ የሚቀርብ ጹሁፍ ብዙዎችን ሊያዘናጋ ይችላል። በዘመናቸው እነ ፕላቶ ለዚህ ነው አጥብቀው በቃላት ድርደራ የሚቀርብን ፣ ነገር ግን ደግሞ የአንድን ህብረተሰብ ችግር ጠለቅ ብሎ ለመመርመር የማያስችልን የሶፊስቶችን ዐይነት የሚመስል አቀራረብ አጥብቀው ይቃወሙ የነበረው።

ከዚህ በተረፈ በየቦታው ብቅ ጥልቅ የሚለው የብሄረ-ሰቦች „የነጻነት ትግል“ ብዙዎችን እያጠያየቀ ነው። ይኸውም በግለሰብአዊ ነጻነትና „በጥቅል ነጻነት“ ላይ የተመሰረተን የተለያየ „ፍልስፍናን“ የያዘ የትግል ዘዴ ወዴት ያመራናል? የሚል ነው። በተጨማሪም ትንሽ ይገባኛል በምለው ኢኮኖሚ ላይም የሚነሳ ጥያቄ አለ። ይኸውም የዛሬው አገዛዝ በአንዳች ነገር ቢወገድ እንኳ የተወሳሰበውን የአገራችንን ችግር በምን መልክ ነው መፍታት የምንችለው? የሚል ነው። ለምሳሌ በገበያ ኢኮኖሚ አማካይነት የአገራችንን የተወሳሰበ የኢኮኖሚና የማህበረሰብ ችግር ለመፍታትና አንድ ጠንካራ አገር ለመገንባት ይቻላል ወይ ? ሌሎችም የተነሱና የሰውን ጭንቅላት ወጥረው የያዙ አሉ። ሁላችንም ለሶስት ቀናት ተገናኝተን ብንደሰትና ሃሳብ ለሃሳብ በመለዋወጥ ለመተንፈስ

Generated by Foxit PDF Creator © Foxit Software
http://www.foxitsoftware.com For evaluation only.

ብንችልም ፣ ጭንቀቱ እንደገና በማገርሸት የሶስቱን ቀን ደስታችንን መና ሊያደርገው እንደሚችል መጠራጠር አይቻልም።

## ለምን የሃሳብ ውዥንብር ይኖራል? ለምንስ የተለያየ ሃሳብ ይኖረናል?

ትዝ እስከሚለኝ ድረስ ድሮው በተማሪው እንቅስቃሴ ዘመንና ከዚያም በኋላ በአብዮቱ ወቅት በአፍላው ላይ እስከዚህም ድረስ ምሁሩን የሚያተራምስ ነገር እምብዛም አለነበረም። የተነሱና የችግሩ ምክንያቶች ናቸው በሚባሉ ነገሮችና ፣ እንዲሁም ከሞላ ጎደል መፍትሄ በሚባሉት ላይ ስምምነት ነበር። ቢያንስ በዘመኑ የተማሪው እንቅስቃሴ መሪዎችን ሊያሰራና እስከተወሰነም ደረጃ መፍትሄ ሊሰጥ የሚችል የተወሰነ የአሰራር ስልት ነበር። መሆን የሌለበት ነገር ተፈጠረና የኢትዮጵያ ህዝብ ህልም መና ሆኖ ቀረ። አብዮትና ሶሻሊዝም የሚባሉ ነገሮች ከጭንቅላታችን ከተወገዱና ፣ በድሮው ታጋዮች ፈንታ አዳዲስ ሃይሎች በመተካታቸው ፣ በድሮው መፈክሮች ፈንታ ሊበራሊዝምና የነጻ ገበያ የሚባሉት ገበያውን በማጥለቅለቅ ሌላ ሁኔታ ውስጥ ከተቱን። በዚህ ላይ ድሮ ግልጽ የነበረው የኃይል አሰላለፍ ከሃያ ዐመት ጀምሮ በግሎባላይዜሽን አማካይነት ደብዛው ስለጠፋና ፣ ሁላችንም በዚህ ውስጥ ገብተን እንድንሽከረከር በመገደዳችን ሀቁን ከውሸቱ መለየት የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጠረ። ግሎባላይዜሽን ፣ አዲሱ ሶሻሊዝምን የሚተካና የዓለምን ማህበረሰብ ሊያስትሳስር የሚችል ሶሻል ፕሮጀክት ነው ተብሎ ቢለፈፍም ከሃያ ዐመት ሙከራ በኋላ የተረፈን ነገር ቢኖር ድህነት ፣ ጥቂት ኃይሎች ዓለምን ማሰስና ከአምባገነኖች ጋር ሆነው በዲሞክራሲ ስም አገዛዞችን በማጠናከር ዕውነተኛ ስልጣኔ እንዳይመጣ እንቅፋት ለመሆን በቁ ። በሌላ አነጋገር ፣ ግሎባላይዜሽንና የነጻ ገበያ አስተሳሰባችንን ከማዘበራረቅና ድህነትን በመፈልፈል አቅመቢስ እንድንሆን ከማድረግ በስተቀር ፣ የጠራ አስተሳሰብ እንዲኖረንና ሰላምን በማስፈን ለስልጣኔ በአንድነት እንድንነሳ ሊያደርጉን አልቻሉም። ስለሆነም ዛሬ ከሃያ ዐመቱ በፊት ከነበረው አስተሳሰባችን ጋር ሳወዳድረው በውዥንብር ዓለም ውስጥ የምንኖር እንጂ የጠራ አስተሳሰብና አመለካከት አለን ብለን ልንዝናና የምንችልበት ወቅት አይደለም። ሰሞኑን በአየር ላይ የሚንዣበበው የፊናንስ ቀውስና በአንዳንድ አገሮች ላይ ዕዳ መቆለል የሚያመለክተው ፣ የዐለማቸን አቅጣጫ ወዴት እንደሚያመራ ገና በቅጡ ያልታወቀ መሆኑን ነው።

ወደኛው አገር ስንመጣ ፣ በተለይም በውጭ አገር ድህረ-ገጾች ላይ የሚወጣውን ጹሁፍ ለተመለከተ በተለያየ ቋንቋ የምንነጋገረና ለተለያየች ኢትዮጵያ የምንታገል ነው የሚመስለው። ቢያንስ በጥልቅ ባለፉት አስራአምስት ዐመታት ባደረጉት ተሳትፎና ክትትል የተመለከትኩትና የተገነዘብኩት ነገር ምሁር ነኝ በሚለው ዘንድ የሃሳብ አንድነትና የመንፈስ ግኑኝነት ለመመስረት አለመቻል ነው። አንድ ጽሁፍ በሚቀርብበት ጊዜ ይነበብና ፣ „የምትለው ትክክል ነው“ ፣ „በርታበት“ ይባልና ፣ ያ እንደዚህ ያለው ሰው መልሶ የራሱን ሌላ ሀተታና ገለጻ ይሰጣል። በዚህ መልክ በአንድ ወቅት የወጣ ጽሁፍ ለጊዜው ተቀባይነት ያገኝ ቢመስልም ፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ደብዛው በመጥፋት ፣ ሌላ አስተሳሰብ ደግሞ ብቅ በማለት የትግሉን ገበያ በማጥለቅለቅ ሌላ ውዥንብር ይነዛል። እንደዚህ እያለ በመቀጠል እልክና ኃይል የሚያስጨርስ ሃሳብ እየተሰነዘረ ካለጊዜያችን እያረጀን መጣን።

አንድ ከስምንት ወር በፊት ባወጣሁት „ ሀቁን መፈለግ ወይስ ሀቁን መናገር“ በሚለው ጽሁፌ ላይ ፣ ስለግሪኩና ስለ አውሮፓው የብዙ መቶ ዐመታት ትግል በተለያዩ ምሁሮች ዘንድ እንዴት የሃሳብ ግኑኝነት መፈጠር እንደቻለና ፣ ምሁራዊ ፈለግን (School of Thought) መከተል ለአውሮፓው ስልጣኔ የቱን ያህል ከፍተኛ አስተዋጾዖ እንዳበረከተ ነው። ለዕውነተኛ ስልጣኔም ሆነ ያንን ለማኮላሸት በኢምፔሪሲስቶች የተደረገው ትግል የተወሰነ የአሰራር ስልትን የተከተለና ዓላማውም ግልጽ እንደነበር ነው። በተጨማሪም አንድ ምሁር አንድ አዲስ ሃሳብ በሚያፈልቅበት ጊዜ ሃሳቡን ማንቋሸሽ ሳይሆን ፣ አይ በማስተካከልና ጥልቀት እንዲኖረው በማድረግ ወደፊት መግፋት ሲሆን ፣ ትክክል ካልሆነ ደግሞ በመተቸትና አዲስ ሃሳብ በማፍለቅ ትግሉን ፈር ማሲያዝ ነበር። እስካሁን እንደተከታተልኩት ከሆነ ፣ በአውሮፓ የረዥሙ የምሁር የትግል ታሪክ ውስጥ በአቦሰጡኝ ወይም ለዝና ተብሎ የተደረገ ትግል አልነበረም። በመጀመሪያ ጥያቄ ሲነሳ ይቀርብ

Generated by Foxit PDF Creator © Foxit Software
http://www.foxitsoftware.com For evaluation only.

የነበረው የትግል ስልት በምን መልክ ነው የሃሳብ ግኑኝነት መፍጠርና ስርዓት ያለው ህብረተሰብ መገንባት የሚቻለው ? በሚለው ላይ ያተኮረ ነበር። ለዚህ ነው በመጀመሪያ በፍልስፍና ላይ በመረባረብ ፣ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ፍልስፍናና ቲዎሎጂን በማስታረቅ ለሳይንስ ቀጥሎም ለቴክኖሎጂ መሰረት መጣል የተቻለው።

አንድ ነገር ግልጽ ለማድረግ ፣ ወደ ኋላ ልመለስና በ60ዎቹ ዐመታት የተማሪው እንቅስቃሴ ሶስት መፈክሮች ይዞ ቢነሳምና ፣ ይህም ለጊዜው ኃይል ለመሰብሰብ ቢረዳውም ፣ ይህ ማለት ግን ይዞ የተነሳው መፈክርና የትግል ዘዴ ሙሉ በሙሉ ትክክል ነበር ማለት አይደለም። ምክንያቱም ትግሉ ጠላት በሚለው ላይ ብቻ ያተኮረ ስለነበር ፣ መሰረታዊ ከሆነ የፍልስፍና ጥያቄ ጋር ለማያያዝ አልቻለም። ስለሆነም በሃሳብ ዙሪያ ትግል ከማድረግ ይልቅ በጉልብት ላይ ብቻ አትኩሮ ተደረገ። በሃሳብ ዙሪያ ትግል ካልተደረገና ፣ ለምንና እንዴት ትግል መደረግ አለበት በሚለው ላይ ሰፋ ያለ ክርክር ካልተደረገ ደግሞ የግዴታ የሃሳብ ግኑኝነት አይኖርም ማለት ነው። በሃሳብ ዙሪያ ትግል ካልተደረገና የሰውን ልጅ ሚናና ተፈጥሮን ምንንት ግንዛቤ ውስጥ ካልተገባ ቡድናዊ ስሜት የመፈጠሩ ጉዳይ የማይቀር ነገር ይሆናል ማለት ነው። ይህንና ወይም ያኛውን ድርጅት ያልደገፈ እንደጠላት ይፈረጅበታል። እንደዚህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ደግሞ የግዴታ የየግለሰቦችን ተፈጥሮአዊ ነጻነት ይነፍጋል ማለት ነው። ግለሰቦች አጥንተው ፣ አውርደውና አውጥተው ይኸኛው ሃሳብና ድርጅት ነው ለአገራችን ዕድገትና ለህዝባችን ተስማምቶ የሰለጠነች አገር ለመገንባት የሚያመቸው መንገድ ነው ብለው ሊቀበሉ እንዳይችሉ ከመጀመሪያውኑ ይታገዳሉ ፤ በፍርሃት እንዲሽማቀቁ ይደረጋሉ ማለት ነው። ይህ ዐይነቱ የትግል ዘዴ ነው እንግዲህ በተለይም በአብዮት አፍላ ወቅት ጎልቶ መታየት የቻለውና ለብዙ መቶ ሺህ ወጣት እህቶቻችንና ወንድሞቻችን መሰቃይትና ካለጊዜያቸው መቀንጠስ ምክንያት የሆነው። እስከዛሬም ድረስ ቁስሉ በደንብ የደረቀ አይመስልም። በመሆኑም በአንድ ወቅት ያዙኝ ልቀቁኝ ፣ ካለኔ በስተቀር ማርክሲስት የለም ይል የነበረው ተስፋ በመቁረጥ አንግቦ ይታገልለት የነበረውን መፈክር በአንድ ጊዜ እርግፍ አድርጎ በመጣል ፣ አይ አንዳንዱ ዕልም ያለ ፀረ-ሶሺልስት ሲሆን ፣ ሌላው ደግሞ ድሮ ይታገላቸው ጋር በመሰልፍ የራሱን ኑሮ መኖር ጀመረ ። በዚህ መልክ ለአንድ ዓላማ እንታገላለን ብሎ የተነሳው ወጣት ተበታተነ።

ኢብዮቱ ከከሸፈና ፣ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ የሃሳብ ጥራት ለማግኘት እምብዛም ሙከራ አልተደረገም። እንዲያውም በባሰ ሁኔታ የሃሳብ መበታተንና በፕርንሲፕል ላይ ያልተመሰረተ ትግል አይሎ ቀጠለ። የአገዛዙን ትክክለኛ ባህርይና ፖለቲካ ፣ የሚከተለውን የኢኮኖሚ ፖሊሲና ፣ ለምንስ እንደዚህ ዐይነቱን ግራ የተጋባ ፖለቲካ ይከተላል? በሚለው ላይ እንታገላለን በሚሉ ተቃዋሚ ኃይሎችና ምሁራን ዘንድ የጠራ አመለካከትና የሃሳብ ግንኙነት በፍጹም ለማዳበር አልተቻለም። አንደኛ ፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ሲመሰረቱ ለመቃወም ያህል ተመሰረቱ እንጂ ፣ ከብዙ ውጣ ውረድና ምሁራዊ ጥናትና ውይይት በኋላ አይደለም የተቋቋሙት። እንዲያውም ፣ ኢብዛኛዎቹ የፖለቲካ ድርጅቶች ዘመናዊ ስም ከመያዝ በስተቀር ፣ ለምን ይህንን ስም ይዘው ይታገላሉ በሚለው ላይ አጥጋቢ መልስ ለመስጠት የሚችሉ አይደሉም። ሁለተኛ ፣ በተያዘው ስም አማካይነት ጠንካራና የተረጋጋ አገር ለመገንባት ይቻላል ወይ? ለሚለው ጥያቄም እንደዚሁ አጥጋቢ መልስ ለመስጠት የሚችል የለም። ይህ ሁኔታ የግዴታ በተለይም ተከታይ ነን የሚሉትን ስም ይዘው እንዲከተሉ ያደረጋቸው ሁኔታ እንዲፈጠር አደረገ እንጂ ፣ የየድርጅቶችን የትግል መሰረትና ፍልስፍና እንዲሁም የትግል ዘዴ በማጥናትና ከራስ ጋር በማዋሃድ አምነው እንዲከተሉ አላበቃቸውም። ይህ ሁኔታ ደግሞ በተለይም የግለሰብን ጊዜያዊ ገናናነትን ለሚያምኑ ጨሌዎች አመቺ ሁኔታ ፈጠረላቸው። በተለይም በምርጫ 1997 የታየው ጉድ ይህ ነው። ቶሎ ወደ ግለሰቦችና ድርጅቶች መጠጋትና ፣ እነሱ ሲዳከሙና ሲፈራርሱ ደግሞ ሌላ መፈለግ።

የዚህ ሁሉ ችግር ምንድ ነው? አንድ ኑርንበርግ ፌስቲቫሉ ላይ ያገኘሁትና ሰፊ የሃሳብ ልውውጥ ካደረግሁት ሰው እንደተገነዘብኩትና ፣ በትክክልም እንዳስረዳኝ ፣ በከፍተኛ ደረጃ ዕውቀትን የሚጠላና ግለሰቦችን የሚያመልክ ኃይል በየቦታው ብቅ ብቅ ብሏል። ይህ

Generated by Foxit PDF Creator © Foxit Software
http://www.foxitsoftware.com For evaluation only.

ዐይነቱ ኃይል በየቦታው በመሰግሰግና ለዕውቀት ዕንቅፋት በመሆን የፖለቲካ ድርጅቶች ጥራት ባለው ምሁራዊ መሰረትና በጥሩ እሴት ላይ እንዳይገነቡ አግዷቸዋል። በተጨማሪም የተለያዩ ድርጅቶችን ለተመለከተ ጊዜያዊ በሆኑ ነገሮች ላይ የሚያተኩሩ ነው የሚመስለው እንጂ ፤ ስትራቴጂዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ጥናት በማድረግ የረዥም ጊዜ የትግል ዓላማ የሚነድፉ አይደሉም። ስለሆነም ፤ መጠናትና በሁሉም ጭንቅላት ውስጥ መያዝ ያለባቸው መሰረተ-ሃሳቦች ፤ ለምሳሌ እንደ ብሄራዊ ነጻነት ጉዳይ ፤ በምን መልክና እንዴት ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባት እንችላለን ፤ የግለሰብ ነጻነት ጉዳይና ግለሰብአዊ ነጻነትን ከጠቅላላው ህዝብ ነጻነትና ፍላጎት ጋር ስለማያያዙ ጉዳይ ፤ ስለ ዲሞክራሲ ምንነትና ጠቅላላው ህዝብ ከተራ ምርጫ ባሻገር በህብረተሰብ ግንባታ ውስጥ ስለሚኖረው ሚና ፤ ስለ ጠንካራ ባህል በመመስረትና ፤ ያሉትን በማደስና በመንከባከብ ላይ መደረግ ስላለበት ጥናትና ውይይት ፤ በአጠቃላይ ሲታይ ባህልና ኪነት አንድን ህብረተሰብ መንፈሱን በማደስና ህብረተሰቡን ለማስተሳሰር ስለሚኖራቸው ሚና ፤ ስለ ማህበረሰብአዊና ፤ በጠቅላላው ስለ ጤንነትና ስለ ወደ ፊቱ የከተማ ግንባታና የመንደሮች አወቃቀር...ወዘተ. እየተነሳ ሰፊ ጥናትና ውይይት አይደረግም። የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ድርጅቶች ካለሰፊ ጥናትና ሀተታ በተራ ፕሮግራምና በነጻ ገበያ አማካይነት ብቻ አንድን ህብረተሰብ መመስረት የሚቻል ነው የሚምስላቸው። እንደዚህ ዐይነቱ አመለካከትና ዕምነት በኛ አገር ብቻ ሳይሆን በብዙ አፍሪካ አገሮችም የተስፋፋና ፤ ለዕውነተኛ ህብረተስብአዊ ግንባታ ዕንቅፋት የሆነና ፓርቲዎችን ወደ ብጥብጥ እንዲያመሩ የሚያደርግ ነው። ብዙዎች ፓርቲዎች አገርንና አንድን ህብረተሰብ እንዴት መገንባት ይቻላል ሳይሆን የሚከነክናቸው ፤ ስልጣን ለእኔ ነው የሚገባው የሚለው ነው። እንደዚህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ደግሞ የአንድን ህዝብ ህልም ያጨልማል። አንድን አገር ወደግብግብ መድረክ እንድታመራ ያደርጋል። ስለሆነም በብዙ አፍሪካ አገሮችም ሆነ በኛም አገርም ጎልቶ የሚታየው ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ድርጅቶች ነን የሚሉና የብሄረ-ሰብ እንቅስቃሴዎችንም ጨምሮ ምሁራዊ መሰረታቸው በጣም ቀጪን ነው ማለት ይቻላል። የተወሳሰበውን ዓለም ለመረዳትና ከውጭ በተለያየ መልክ የሚመጣውን ግፊት ለመቋቋም የሚያስችላቸው ምሁራዊ ኃይላቸው በጣም ደካማ ነው።

በዚህ ዐይነት የተዘበራረቀ ሁኔታ ውስጥ የምሁሮች ሚና ትግሉ ጥራት እንዲኖረው ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ነበር። ባልሳሳት ፤ እንደማየውና እንደምከታተለው ከሆነ የያዝ ለቀቅ ትግልና ፤ በአንድ ወቅት አንዱን ፤ በሌላ ወቅት ደግሞ ከሁኔታው ጋር ሊጓዝ የማይችል ሀተታ በማቅረብ ትግሉን ማዘበራረቅ እንደሙያ ተይዟል። እንደዚህ ዐይነቱ የትግል ዘዴ ታምኖበት ይሁን ፤ ወይስ ግራ በመጋባት የሚቀርብ ሀተታ መሆኑን ለመናገር ያዳግታል። ባጭሩ ግን እንደዚህ ዐይነት ግራ የተጋባ ሀተታ በሚቀርብበት ወቅት ሀተታውን በሚቃወሙና ትክክለኛ ነው ብለው በሚከተሉት መሀከል እንደገና የማያስፈልግ ግጭት ይፈጠራል። በተለይም ነገሮቸን በጥቁርና በቀለም በመለየት ብቻ አመኔታ በሚገባበት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ትግሉ „አርቀው በሚያስቡና በማያስቡ" መሀከል የሚደረግ የሚመስላቸው አሉ።

ነገሩን ተጨባጭ ለማድረግ ፤ ሰሞኑን በድህረ-ገጾች ላይ የሚወጣውን ከኢህአዴግ ጋር አብሮ ስለመስራት ጉዳይ ፤ ወይም ስለመቻቻል ጉዳይና አገሪቱን ከሚጠብቃት ጨለማ ለማዳን መደረግ ስላለበት ጉዳይ ሳነብ ሌላ ዓለም ውስጥ ያለሁ ነው የሚመስለኝ። ይህንን ጥያቄና የሚያነሱና ሀተታ የሚሰጡ ኢህአዴግን ለማባበል የተደረገውን የሃያ ዐመቱን ትግል አልተመለከቱም ወይ ? አንድ ላይ እንስራ ቢባልስ ራሱ ኢህአዴግ ሊቀበለው ይችላል ወይ? ባህርዩስ ይፈቅድለታል ወይ ? ከዚህ ቀደምስ ይከተላቸው የነበሩትን ፖለቲካዎች አንድ ባንድ መቀልበስና ማስተካከል ይችላል ወይ? ከመቅሰበት ወደ መቶ ሰማንያ ዲግሪ በመቀየርና አምላክ በመሆን ፤ እስከዛሬ ድረስ አጥፍቼያለሁና ተባብረን በአምላክ ፈቃድ ይህችን አገር ከጥፋት እናድናት ሊል ይችላል ወይ ? በተጨማሪም ፤ እስከዛሬ ድረስ የገነባውን የጸጥታ ኃይል በማፈራረስ ተቃዋሚው ኃይል ካለምንም ፍርሃት ሃሳቡን ለህዝብ እንዲገልጽ ማድረግ ይችላል ወይ ? ሌላው መነሳት የሚገባው ጥያቄ ፤ አገዛዙ ሃያ ዐመት ያህል ለምን እንደዚህ ዐይነቱን ፖለቲካ ተከተለ? ተገዶ ወይስ አገርን ለማዳከም ካለው ፍላጎት? ይህንን

Generated by Foxit PDF Creator © Foxit Software
http://www.foxitsoftware.com For evaluation only.

ነው እንግዲህ ስለተባብሮ መስራትና መቻቻልን ስለሚያነሱትና ስለሚወተውቱት እህቶቻችንና ወንድሞቻችን እንዲያስረዱን በክብር የምንጠይቃቸው። በሌላ ወገን ግን ግልጽ የማድረገው አንድ ነገር አለ። እስከማውቀውና እስከተከታተልኩት ድረስ ፣ በማንኛውም አገር ታሪክ ውስጥ ስልጣን ላይ ወጥቶ ከውስጥ አገርን ያዳከመና የህዝብን ሃሞት እንዲፈስና በዓለም ላይ መሳቂያና መሳለቂያ ያደረገ እንደ ወያኔ አገዛዝ በፍጹም የለም። ሂትለር ራሱ እንኳ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ሲጨርስ ጀርመንን ከሁሉም አገሮች በላይ አደርጋለሁ ብሎ ተነሳ እንጂ ፣ ጀርመንን ዝቅ አድርጌ ደካማና ለማኝ አደርጋለሁ ብሎ በፍጹም አልተነሳም። እዚህ ላይ እንዲያዝልኝ የምፈልገው ፣ የሂትለርን ግፍ ለመደገፍ አይደለም። ማወዳደሩ ምናልባት አንዳንዶችን ሊረብሻቸው ይችል ይሆናል። የብሄራዊ ነጻነትንና የአገርን ምንነት ለሚረዳ ግን ነገሩ ግልጽ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

በዕውነቱ „በተቃዋሚውና“ ወይም ደግሞ በኢህአዴግና በሰፊው የኢትጵያ ህዝብ መሀከል ያለው ትግል እስከዛሬ ድረስ አሰቃይተኸናል ፣ ረገጠኸናል ፣ አዋርደኸናል ፣ አገራችንን ሸጠኸብናል ፣ በአጭሩ ተፍጥሮአዊ ነጻነታችንን ገፈህናልና ይብቃህ ፣ ከጫንቃችን ላይ ውረድ የሚል ነው። ጠቡ በባልና በሚስት መሀከል ያለና ፣ እስከዛሬ ድረስ ብዙ ልጆች ወልዳችሁ ፣ የልጅ ልጆች አይታችሁ ፣ አሁን ምን ያጣላችኋል ፣ ለምንስ ትፋታላችሁ ? ብሎ ለማስታረቅ የሚደረግ ዐይነት ልምምጥ አይደለም። ትግሉ የፍልስፍና ጥያቄ ነው። ትግሉ አንድን ህብረተሰብ በፀና መሰረት ለመገንባትና ህዝባችን በመፈቃቀርና በመከባበር እጅ ለእጅ ተያይዞ የጋራ አገር ለመገንባትና ለተከታዩ ትውልድ ለማስተላለፍ በሚታገለው መለው የኢትዮጵያ ህዝብና ፣ ይህንን የአንድን ህዝብ ህልምና ምኞት አጥብቆ በሚቃወመው መሀከል ነው። ትግሉ ተቃዋሚ ነኝ ብሎ እዚህና እዚያ በሚረረጠውና በወያኔ መሀከል አይደለም። ስለዚህም የመቻቻልና ያለመቻቻል ጉዳይም አይደለም። ትግሉ የክብርና የነጻነት ጉዳይ ነው። ትግሉ የአገር ህልውና ጉዳይ ነው። ስለዚህም ትግሉ የታሪክን አደራ ለመቀበል በተዘጋጁና ፣ ውድ እናት አገራችንን በዓለም ውስጥ ክብር ቦታዋን እንድታገኝ ከዘለዓለማዊ ጦርነትና ረሃብ ለማላቀቅ የሚደረግ ነው። ይህንን የተቀደሰ ዓላማ ነው አቶ መለሰና የተቀሩት ወያኔዎች አጥብቀው የሚጠሉት። እንደዚህ ዐይነቱን ጥላቻቸውን አለማየት መቻልና ፣ እስካሁን ድረስ የሰሩትንና የሚሰሩትን ወንጀል ለመረዳት አለመቻል ፣ ይቅርታ ይደረግልኛን ፣ እንደ ዕውርነት ይቆጠራል።

ይህ ከላይ የተዘረዘረው ሰሞኑን ድህረ ገጾችን ከሞላ ጎደል ያጠበበው ጉዳይ ሲሆን ፣ ለእንደኔ ላለው ተራ ተከታይ ግራ የሚያጋቡ ሌሎች ጉዳዮችም አሉ። በመጀመሪያ የተለያየ የቤት ዐይነት- ለምሳሌ የሳር ቤት ፣ የቆርቆሮ ቤት ፣ በብሎኬት ወይም በጡብ የሚሰራ ቤት-ለመስራት ነው የምንታገለው ካልተባለ በስተቀር ፣ አንድና ጠንካራ አገር መገንባት አለብን ከተባለ የምንክተለው መሰረተ-ሃሳብ አለ። እንዲያው ትግሉ ሊበራሊዝም ይሻለናል ፣ የነጻ ገበያ ያዋጣናል ፣ ከዚህኛው ወይም ከዚያኛው አገር ጋር ብንሆን ይሻለናል በማለት ምርጫን የማቅረቡ ጉዳይ ሳይሆን ፣ ህዝባችንን ዕውነተኛ ነጻነት ሊያጎናጽፈውና ዘለዓለማዊ ሰላም ሊሰጠው የሚችለው ሳይንሳዊው መንገድ የትኛውን መንገድ ነው መከተል ያለብን? በሚለው ላይ ነው መወያየት የሚኖርብን። እስከዛሬም ድረስ ያለው ችግር አንድ የተወሰነ ሃሳብ ወስዶ እሱን ማብላላትና እስከመጨረሻው ድረስ መጓዝ ሳይሆን ፣ ወዲህና ወዲያ መፈናጠር ነው ሁላችንንም ግራ የሚያጋባው። ለመስራት የምንፈለገውን ቤት ካላወቅንና ፣ በምን ማቴሪያሎች መስራት እንዳለብን እስካልተገነዘብን ድረስ ደግሞ ትግላችን የተምታታና ፣ በጉጉት አንድ ዐይነት ነገር ለሚጠባባቀው ህዝባችን የተስፋ ጭላንጭል ለማሳየት አንችልም ማለት ነው። ከዚህ ውዥንብር መውጣት አለብን። ስለዚህም የትኛውን መንገድ መያዝ አለብን ፣ ወይም መከተል ይኖርብናል ብለን በፕርንሲፕል ደረጃ የምንወስዳቸው ነገሮች አሉ። ከራሳችን ፍላጎት የመነጩ ሳይሆኑ ፣ ኢትዮጵያንና የህዝቦቿን ዕድል የሚመለከቱ መሆን አለባቸው። ግልጽና ማንኛውም ተራ ሰው ሊረዳው የሚችለው መሆን አለባቸው። እስከዛሬ ድረስ በዓለም ላይ ለሶስተኛው ዓለም ተብለው የቀረቡት የህብረተሰብ ሞዴሎች በሙሉ ፀረ-ሳይንስ ፣ ፀረ-ስልጣኔና ፀረ- የሰው ልጅ ናቸው። ተፈጠሮን የሚቀናቀኑና ወደ ተራ በዝባዥነት የለወጡና የሚለውጡ ናቸው። ከዚህ ዐይነቱ ረባሽ ሞዴል መላቀቅ አለብን። በመጀመሪያ ግን የረባሹን ሞዴል የርዕዮተ ዓለምና የቲዎሪ መሰረት መረዳት ያስፈልጋል። የጠላትን የትግል ስትራቴጂ በደንብ ሲረዱ ነው አዲስና

Generated by Foxit PDF Creator © Foxit Software
http://www.foxitsoftware.com For evaluation only.

በፕሪንሲፓል ላይ የተመረኮዘ የአሰራር ዘዴና መፍትሄ መፈለግ የሚቻለው። ይህንን ስናደርግና የተሻለ ስናገኝ በእርግጥም ለህዝባችን ቀናውን መንገድ ማሳየት እንችላለን ማለት ነው።

ይህ ማለት ግን ግትር ያለ ሃሳብ እንከተል ማለትም አይደለም። አንድ ህብረተሰብ ተለዋዋጭና ወደፊትም እየተወሳሰበ ሰለሚመጣ ከሁኔታው ጋር የሚጓዙ ነገሮች ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ግልጽ መሆን አለበት። ይሁንና ግን መሰረታዊው ሃሳባችን ህዝባችንን የሚረብሽ መሆን የለበትም። ግልጽና ሎጂካዊ መሆን አለበት። ከፍርሃትና ከይሉኝታ ውጭ መሆን አለበት። ቡድናዊ ስሜትንና እልከኝነትን ያስቀደመ መሆን የለበትም። ስለሆነም በዕርግጥ ለአገራችን ነጻነት የምንታገለን ከሆነ ጭንቅላታችንን ከተንኮልና ካላስፈላጊ ጥርጣሬ ማጽዳት አለብን። መተማመን መቻል አለብን። ዕውነተኛ አገር ወዳድነትን ከሰውነታችን ጋር ማዋሃድ አለብን። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ኢትዮጵያ ፣ በዚያች አገር ውስጥ የተወለዱና ያደጉ ፣ እንዲሁም የሚኖሩ ዜጎች ሁሉ አገር ናት የሚለውን መሰረተ-ሃሳብ በጭንቃላታችን ውስጥ መቅረጽ አለብን። ስለዚህም ስንወያይና ስንከራከር ፣ ስለታልንቱ ሁኔታ ሳይሆን ፣ ስለዛሬይቱና ስለወደፊት ኢትዮጵያ ነው መነጋገር ያለብን። ስለዚህ ታሪክን እየቆፈርን እያወጣን የመወያያ አጀንዳ የምናደርግ ከሆነ ከዘለዓለማዊ ንትርክና ብጥብጥ አንላቀቅም ማለት ነው። የብሄረ-ሰቦች ጭቆና ፣ የብሄረሰቦች ነጻነት እያልን የምንታገል ከሆነ እስከዛሬ ድረስ እንዳደረግነው ሁሉ ከሳይንስና ከዕውነተኛ ስልጣኔ እየራቅን ዘለዓለማችንን ፍዳችንን እናያለን።

በአውሮፓ የህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ የተደረገው ትግል የብሄረ-ሰብን ትግል በማስቀደም አልነበረም። ብሄረሰቦች ወይም ጎሳዎች አልነበሩም ማለት አይደለም። ትግላቸውን ፣ በፍልስፍና ዙሪያና ፣ በሃይማኖት ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ዙሪያ ፣ በአጭሩ ቀስ በቀስም የየግለሰቦችን ነጻነትና ሚና አጉልቶ በማሳየትና አንድ ህብረ-ብሄር(Nation-State) ለመገንባት የተደረገ ትግል ነው። ትግሉ የሰውን ልጅ ሚናና የተፈጥሮን ትርጉም ተረድቶ ፣ በተፈጥሮ ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ ነገሮችን በማውጣትና ቅርጻቸውን በመለወጥ አዲስ ህይወት ለመመስረት የተደረገ ትግል ነው። ስለሆነም ከግሪኩ ስልጣኔ አንስቶ እስከ አውሮፓው የነካንትና ሺለር ዘመን ድረስ የተደረገው ትግል ጭንቅላትን በማጽዳት መንፈሳዊና ማቴሪያላዊ ነገሮቸን በማዋሃድ የሰውን ልጅ ሚና አጉልቶ በማሳየት ዕውነትኛ ስልጣኔን ለማምጣት ነበር ። የአውሮፓው ስልጣኔ ዛሬ ዓለምን በሚያስሱና ወደጦርነት አውድማ ለመለወጥ በሚቅብዘበዙ ኃይሎች አይደለም የተነጠፈው። የስልጣኔው መሰረት የተጣለው ሰብአዊነትን ከደማቸው ጋር ካዋሃዱ ፣ ጥልቅ ዕውቀት ከነበራቸውና ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ ፣ ይሁንና ደግሞ የቴክኖሎጂን አጠቃቀም የሰውን ልጅ ፍላጎት ለማሟላት ከሚያስፈልገው ባሻገር አልፎ መሄድ እንደሌለበት በተገነዘቡ ፣ ወደ እግዚአብሄር የሚጠጉ በሚመስሉ ታላላቅ ሊቃውንት ነው የተጣለው። የዛሬው አውሮፓ ካለፕላቶንና የሱን ፈለግ ይዘው በኋላ ከተነሱት ፣ ቄስ ኩዛኑስ ፣ ኬፕለር ፣ ጋሊልዮ ፣ ዳቪንቺና ላይብኒዝ ፣ ጋውስ ሪማን ፣ ቀጥሎም ደግሞ ካንትና ሺለር እንዲሁም ሌሎች ዕውነተኛውን ነገር ከመፈለግ በስተቀር በጭንቅላታቸው ውስጥ ምንም ዐይነት ተንኮል ባልነበራቸው ታላላቅ ምሁራን ነው የተዘጋጀው። ባጭሩ የአውሮፓው ህብረ-ብሄርን የመመስረቱ ትግል ውጣ ውረድ የበዛበት ቢሆንም ፣ የዛሬው ቦታ ሊደርስና ዓለምን ለመቆጣጠር የቻለው በትንሹ በማሰብ አይደለም። ትግሉን በሁሉም አቅጣጫ በማድረግና ፣ ይሁንና ደግሞ መልክ እንዲኖረው በማድረግና የተሰበጣጠረው አስተሳሰብ እንዲሰበሰብና ለስራ እንዲነሳሳ በማድረግ ብቻ ነበር።

## የኛ ችግር ካለትምህርተ አስተሳሰብ(School of Thought) ትግል ማካሄድ ነው!

በአውሮፓ ምሁራዊና ማህበረሰብአዊ እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ ቲዎሪ ፣ የተወሰነ የአሰራር ስልትና(Methodology) ርዕይ ወሳኝ ሚናን ተጫውተዋል። ቲዎሪ በተጨባጭ ነገሮች ላይ ተመስርቶ ትንተና ለመስጠት የሚደረገበት መሳሪያ ሲሆን ፣ በአንዳች ዐይነት ቲዎሪ አንድን ሁኔታ ለመገምገም ደግሞ የተወሰነ የአሰራር ስልትን ወይም የፍልስፍናን ፈለግ መከተል ያስፈልጋል። ካለቲዎሪና ካለፍልስፍና በአንድ የተወሰነ ወቅት የሰፈነን የተዘብራረቀንም ሆነ ከሞላ ጎደል ተስተካክሎ የሚገኝን ህብረተሰብአዊ ሁኔታም ሆነ

Generated by Foxit PDF Creator © Foxit Software
http://www.foxitsoftware.com For evaluation only.

የሰዎችን መንፈስና አሰራራቸውን ለመረዳትና ግምገማ ሰጥቶ መፍትሄ ለመጠቆም በፍጹም አይቻልም። ሰለሆነም በአውሮፓ የህብረተሰብ ግንባታ ታሪክ ውስጥ ምሁራዊ ውይይት(Discourse) መሰረታዊ ቦታ ይይዛል። እንደዚህ ዐይነቱ ምሁራዊ ውይይት ለቅንጦት የሚደረግ ሳይሆን በጊዜው በየአገሮች የሰፈነውን የጨለማ ሁኔታና የገዢዎችን የአገዛዝ ስልት ለመረዳት የተለያዩ ምሁሮች እንደየአመለካከታቸው የግዴታ ያፈለቁት ተጨባጭ ሁኔታዎችንና የሰዎችን የማስብ ኃይል የመመርመሪያ ዘዴ ነው። አንድ ምሁር አዲስ ሃስብ ሲሰነዝር ፣ አዲሱ ሃስብ ትክክል መስሎ ያልታየው ደግሞ የለም ይህ ትክክል አይደለም ብሎ የራሱን ትክክል ነው ብሎ የሚገምተውን ሃሳብና የአሰራር ስልት ይሰነዝራል። ከሰነዘረ በኋላ ግን ለምን እንደዚህ አደረግ ተብሎ የስድብ ውርዥብኝ ወይም የፍየል ወጠጤ ዘፈን አይዘፈነበትም። አብዛኛውን ጊዜ ተቃውሞ ይመጣ የነበረውና አንዳንድ ምሁራንን እንዲሰደዱ ወይም እንዲገደሉና እንዲታሰሩ ያደርጋቸው የነበረው ቀድሞውኑ በሃይማኖት መሪዎችና በግዢ መደቦች ተቀባይነት የነበረው ዶግማ በጥያቄ ውስጥ ሲገባ ብቻ ነበር። ይሁንና በድፍረት የተደረገው ትግል ወደድንም ጠላንም የሃማኖትን ዶግማ በማሸነፍ ለሳይንሳዊ አስተሳሰብ ቦታን እንዲለቅ ተገደደ። ስለሆነም ከዚያም በፊትም ሆነ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ በአሸናፊነት ከወጣበት ከአስራአምስተኛው ክፍል-ዘመን ጀምሮ የተለያዩ የአስተሳሰብ ፈለጎችን ተከትሎ ተፈጥሮን መቃኘትና አዲስ ህብረተሰብን ለመመስርት መታገል መሰረታዊ የአውሮፓ ምሁራዊ የትግል ዘዴ ሆነ። የኋላ ኋላ ደግሞ ቀድሞ የነበረው ሰፉ ያለውና ሳይንሳዊው መንገድ በርዕዮተ-ዓለም ሽፋን ስር ደብዛው እየጠፋ መጣ። ሶሻሊዝም ከፈራረሰ በኋላ የገበያ ኢኮኖሚና ሊበራሊዝም በሚለው ግን ደግሞ አንድን ተጨባጭ ሁኔታ ለመተንተን ሊረዳ በማይችለው ርዕዮተ-ዓለም እየተተካ መጣ። ዓለም ወደ አንድ አቅጣጫ እያመራች ነው ፣ የሚለው ግን ደግሞ የተዘበራረቁ ሁኔታዎችን ለመረዳት የማያግዘው ቀስ በቀስ ወደ አእምሮ በመግባት ዕውነትን ከውሸቱ ለመለየት የማያስችልበት ሁኔታ ተፈጠረ። በዓለም ታሪክ ውስጥ የኃይል አሰላለፍ እንደሚለዋወጥ ሁሉ የሰውን ጭንቅላት የሚይዙና ከትክክለኛው ፈር እንዲወጣ የሚያደርጉ ዶግማዎችም በዚያው መልክ በመዳበርና ለቅስቀሳ መሳሪያ በማገልገል የሰውን ልጅ የስልጣኔ ጥማት ለረዥም ጊዜ ተንጠልጥለው እንደሚያቆዩ የታወቀ ጉዳይ ነው። ዛሬን ያለንበት ይህንን ነው የሚመስለው።

ወደኛ አገር እንደገና ተመለሰን ስንመጣ ይህንን በየጊዜው እየተፈራረቀ ብቅ የሚለውንና ውዥንብር የሚነዛውን ርዕዮተ-ዓለም ለመረዳት የሚያስችለን የቲዎሪ መሳሪያ በየተማርነው ትምህርት አማካይነት ለማዳበር አለመቻላችን ነው። ዓለምን በጥቁርና በነጭ በመሳል ፣ ወይም ደግሞ በሌላ በጣም ጠባብና በምንም ዐይነት ለሳይንስ የማያመች የትግል ዘዴና የአጻጻፍ ስልት በመከተልና እንደየሁኔታው በመቃየየር ግራ የተጋባንበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው ብል እንደ አዋቂነት እንደማይቆጠርብኝ ተስፋ አደርጋልሁ። በሌላ ወገን ደግሞ ተማርኩ ፣ አውቃለሁ የሚል ሰው እሱ ከሚያሰበውና ፣ የተሳሳተም ቢሆን ከሚከተለው ዶግማ በተለየ መልክ የሚቀርብን አስተሳሰብ በፍጹም ሊቀበል አይችልም። ምክንያቱም የሚሸነፍ ይመስለዋል ፤ ወይም ደግሞ እንደ ቀድሞዎች የካቶሊክ ቄሶች አመለካከት የአሳሳስችና የሰይጣን ስራም የሚመስለው አለ። በዚህ መልክ ሃሳብ ጥራት ከማግኘት ይልቅ ችግር ቢደራረብና በድሮም መሳሪያ መፍታት እንደማይቻል „ቢታወቅም“ በዚያው የሚገፋ ምሁራዊ ኃይል አለ።

እንደዚህ ዐይነቱ ግትር አስተሳሰብ ለምንድነው ጸንቶ የሚቆየው? ከራሴ ልጀምርና ትምህርት ዓለም ውስጥ ከገባሁ ከህጻንነቴ ጀምሮ ዶክትሬት ዲግሬይን እስካገኝ ድረስ ፣ አገር ፣ ብሄራዊ-ነጻነት ፣ ህብረተሰብና አንድ ህብረተስብ እንዴት ሊገነባ ይችላል? ምን ምንስ ቅደመ-ሁኔታዎች ያስፈልጋሉ? ፣ ባህልና የባህል ተሃድሶ አስፈላጊነት ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የአንድን ህብረተ-ሰብ ችግር ለመቅረፍ ሰለሚኖራቸው ሚና... ወዘተ. እየተባለ በተያያዘ መልክ የተማርኩት ነገር አልነበረም። ቀደም ብሎ ደግሞ የተወሰነ ርዕዮተ-ዓለምን ብቻ „በመከተል“ ለፍልስፍናና ለሳይንስ ቦታ ሳልሰጥ ዓለምን በጥቁርና በነጭ ብቻ እየሳልኩ የምመለከትበትና የምዝናናበት ዘመን ነበር። እኔም ብቻ ሳልሆን ፣ ከኔ ቀደም ብለው የሄዱና የዕውቀትን የመጨረሻውን ቁልፍ የያዙ የሚመስላቸው የሚኩራሩበትንም ጊዜ

Generated by Foxit PDF Creator © Foxit Software
http://www.foxitsoftware.com For evaluation only.

ተመልካቸለሁ። ከዚህ አንድ ወጥ አስተሳሰብ ለመላቀቅና ፣ ትምህርት ቤትስ የተማርኩት ትምህርት በርግጥ ለአንድ ህብረተሰብ ግንባታና ለዕውነተኛ ስልጣኔ ሊያገለግል ይችላል ወይ? የሚለውን ጥያቄና መልስ ለመፈልግ የተወሰነ መስዋዕትነት መክፈል ነበረብኝ። ከሌሎች ስቃዮች ጋር ተደምሮ ፣ በአገር ልጆች መሰደብንና መናቅን ፣ በአጭሩ የህሊና ቶርቸርን መቋቋም የግዴታ ያስፈልግ ነበር። ምክንያቱም ቀላል ነው። በየቦታው የተሰገሰጉ ፣ በአንድ በኩል ለአገር ተቆርቋሪ የሚመስሉ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ እዚያው በዚያው የህዝባችንን ስልጣኔና የአገራችንን ጥንካሬ አጥብቀው የሚጠሉ የውሸት ወሬ በማራገብ ለመነጠልና ለማስመታት ያላደረጉት ጥረት አለነበርም። እነዚህ ዐይነቱ ግለሰቦች ደግሞ ከደሃው ኢትዮጵያዊ አብራክ የፈልቁ አይደሉም። በማርክሲስቶች አባባል የመደብ ንቃተ-ህሊና(Class Consciousness) ያዳባሩና የታሪክን ሂደት ለማጣመምና የህዝቦችን ዕውነተኛ ነጻነት አጥብቀው በሚጠሉ ነበሩ። ዛሬም አሉ።

ያም ሆነ ይህ ፣ ይህ ዓይነቱ በተወሰነ ርዕዮተ-ዓለምና ጠባብ አመለካከት መጠመዱ በአንድ የተወሰነ ወቅት የገባንበት ወጥመድ ነበር። በአንዳንዶቻችን ዘንድ አሁንም ቢሆን በዚያው የቀረንና የአንድን ህብረተሰብ የርዥም ጊዜ ውጣ ውረድ ጉዞ በሰፊው ለማጥናትና ለመመልከት የማንፈልግ ፣ ወይም ደግሞ የማንችል አለን። አንድ ሁላችንንም የሚያገናኙ ነገሮች እንዳሉ የዘነጋንና ፣ የታሪክ ኃላፊነት እንዳለብን ያልተረዳን ምስኪኖች በየቦታው ተበታትነን እነገኛለን። በዚያው መጠንም በዕድሜያችን እየገፋን በሄድን ቁጥር ፣ ጊዜ ምን ያህል ጠቃሚና ቶሎ ቶሎም በፍጥነት እንደሚሄድ የማንረዳ ብዙዎች ነን። ስለሆነም በሆነው ባልሆነው በመጠመድና በጠባብ ዓለም ውስጥ በመሽከርከር ጊዜ እየሰራብን እንጂ ፣ በጊዜ እየተጠቀምነበት አይደለም። ከእንደዚህ ዓይነቱ የሃሳብ ግትርነትና ውዥንብር ለመላቀቅ ፣ በአንድ በኩል ራሳችንን መጠየቅና ራሳችንን ማግኘት አለብን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ለህዝባችን እንታገላለን የምንል ከሆነ የዛሬውን የህብረተሰባችንን ሁኔታና በምንስ መሰረት ላይ ነው መገንባት ያለበት የሚለውን? ማውጣትና ማውረድ አለብን። አንድን ህብረተሰብ ለመገንባት የሚያገለግል የማቲማቲክ ፎርሙላ የለም። ይሁንና ግን በጭንቅላት መቋጠራና እንደ መሰረተ-ሃሳብ መወሰድ ያለባቸው ነገሮች አሉ። እንደሚታወቀው አንድ ህብረተሰብ ማንም እየተነሳ እንደፈለገ የሚወራጭበት ወይም የሚዋኝበት መድረክ አይደለም። ማንኛውም ህብረተሰብም ሆነ እያንዳንዱ ግለሰብ ፣ ሞራላዊ ፣ እሴታዊ ፣ ጥበባዊና በአጨሩ ታሪክ የሚሰራበት መድረክና እያንዳንዱም ግለሰብ እንደችሎታዊ ታሪክ ሰሪ ነው። ለዚህ ደግሞ የተወሰነ በየጊዜው እንደ አየሩ ሊለዋጥ የማይችል ፍልስፍና ወይም ፕሪንስፐልስ ያስፈልጋል። ችግርን ፈጣሪ ሳይሆን ፣ ችግርን በደንብ መመርመር የሚያስችልና መፍትሄም ለመጠቆም የሚረዳ መሆን አለበት።

ከላይ እንዳልኩት ከአንድ አሰራር ዘዴና ፍልስፍና እጦት ወይም ለመከተል ካለመፈለግ የተነሳ የተለያዩ ቤቶች ፣ ግን ደግሞ በቀላሉ በውሃ ሙላት ፣ በመሬት መንቀጥቀጥና በነፋስ ኃይል ተጠራርገው ሊወሰዱ የሚችሉ ቤቶችን ለመስራት የምንታገል ነው የሚምስለው። ለምሳሌ ከላይ ያነሳሁትን በሶስት ግለሰቦች የተሰነዘረውን አስተሳሰብ ትተን ወደ አጠቃላዩ የህብረተስብአችንን አወቃቀር ታሪክ በአንዳንዶች የሚሰነዘረውን ስሰማ በፍጹም ለሳይንስና ለስልጣኔ የማያገለግል ፣ ዘለዓለማችንን እየተናቆርን እንድንኖር በሚያደርጉን ላይ ነው የምንረባረበው። በመጀመሪያ ደረጃ ማንኛውም ህብርተሰብ የተወሳሰበ እንደመሆኑ መጠን ፣ እንደየህብረተሰቡ ንቃተ-ህሊና ይኸኛውን ወይም ያኛውን መንገድ ይዞ ሊጓዝ ይችላል። በአጠቃላይ ግን በዓለም ላይ የሚገኙ ማህበረሰቦችን የሚያገናኝ ፎርሙላ የሚመስል ነገር አለ። ይኸውም ማንኛውም ህብረተሰብ ከትንሽ ሁኔታ በመነሳት በመስፋፋትና በማደግ እንደህብረተሰብ ይገነባል።ከአንድ የተወሰነ የታሪክ ወቅት በኋላ አንድ ርዕይ እየያዘ እንዲመጣ ይገደዳል። ማንኛውንም ህብረተሰብ እንደ ባዮሎጂካል ክንውን(Biological Process) መመልከት ያስፍልጋል። አንድ ተፈጥሮአዊ ነገር ፣ ለምሳሌ አንድ የዛፍ ዓይነት ለማደግ የግዴታ አስፍላጊው ንጥረ-ነገሮች ፣ ፀሃይና ዝናብ በበቂው ተሟልተው ሲገኙ ማደግና መፋፋት ይጀምራል። እንደዚሁም አንድ ህብረተሰብ አስፈላጊውን ንቃተ-ህሊና ካገኛና የፖለቲካ አየሩም አመቺ ከሆነ አዳዲስ ሃስቦችን ለማፍልቅ ፣ የስራ-ክፍፍልን ለማዳበርና ፣ ከክልሉ አልፎ በንግድ አማካይነት የባህል

Generated by Foxit PDF Creator © Foxit Software
http://www.foxitsoftware.com For evaluation only.

ግኑኝነት ያደርጋል። ይጋባልም ፣ በመዋለድም እየተሳሰረ ይመጣል። ይህ ተፈጥሮአዊና ህብርተሰብአዊ ህግ ነው። ይሁንና ግን የማሰብ-ኃይል ባልዳበረበትና የማቴሪያል ሁኔታዎች አመቺ ሆነው በማይገኙበት አገር ውስጥ የአንድ አገር ዕድገት ቀጥተኛ መንገድ ይዞ ሊጓዝ አይችልም። በህበረተሰብ ታሪክ ውስጥም ፣ በተለይ ትላልቅ አገሮችን ብንወሰድ ካለደም መፋሰስና ካለጉለበት እንደ ህብርተሰብ የተገነባ አገር በፍጹም የለም። አንድ አገር እንደ ህብረተሰብ መገንባት የለበትም ፣ ሁሉም በየጎጆው እየተከለለ ይኑር ካላልን በስተቀር ፣ ህብረተስቦች የተጓዙበት ሂደት ልዩ ልዩ መልክ ቢይዝም አነሰም በዛም ቀደም ብሎ የሄደው የህብረተሰብ ክፍል ሌላውን በማስገደድም ሆነ በጋብቻና በልዩ ልዩ ነገሮች በማባበል ወደ ትልቅነት ለመሸጋገር ተችሏል። ከብዙ የዓለም ማህበረሰቦች የአውሮፓውን ነጥለን ስንመለከት ፣ ሬናሳንስ ለተለያዩ የአውሮፓ አገሮች እንደ ህብረ-ብሄር እንዲገነቡና ፣ አንድ ቋንቋ እንዲናገሩና ፣ በአንድ ባንዲራና በአንድ አገዛዝ ጥላ ስር እንዲወደቁ አመቺ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል። ስለሆነም በተለያዩ የአውሮፓ ህብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ጎሳዎች እየተዋሃዱ ከሄዱ በኋላ እንደገና ተመልሰው የናታቸው ማህፀን ውስጥ እንግባ ብለው አመጽ አልጀመሩም። በተመሰረተው ህብረተሰብ ውስጥ ብቻ ነው ግለሰብአዊ ነጻነትን ለመቀዳጀትና የራስን ብቃትነት ለማሳየት የታገሉት። ለምሳሌ በጀርመን የህብረተሰብ አመሰራረትና ግንባታ ውስጥ ለጀርመኖች ዐይን መክፈትና ማደግ አይሁዶች የማይናቅ ሚና ተጫውተዋል። አይሁዲዎች ጀርመን ውስጥ ራሳችንን ነጻ ማውጣትና ነጻ አገር መመስረት አለብን ብለው በፍጹም አልታገሉም።

ሰሞኑን ስለ ብሄ-ረሰቦች ታሪክና ትግል የሚነሳውን ጭቅጭቅ ስሰማና ስመለከት እንደገና በስድሳኛዎቹ ዘመን ይደረግ እንደነበረው-በጊዜው አልነበርኩም- ወደ ኋላ ተመልሰን ሌላ ታሪክ ለመስራት የምንታገል ነው የሚመስለኝ። እነ አቶ መለስ ስልጣን እንደያዙ ሰሞን የየብሄረ-ሰቡ ተጠሪ ብቻ ሳይሆን ፣ በትምክህተኝነትና በጨቋኝነት የሚታማው ራሱ የአማራው ብሄረ-ሰብ ተወካይ ሁሉ ሳይቀር „ከዚህች ባንዲራ በስተጀርባ ብዙ ግፍ ተፈጽሟል" እያለ ነበር የሚያራግበው። አሁን ደግሞ „በታሪካችን ውስጥ ብዙ ጉድፎች ታይተዋል" ፣ „አፄ ምኒልክ ኢትዮጵያን አንድ አድርገው ለመግዛት ማንኛውንም እርምጃ ወሰደዋል" ፣ እየተባለ ካለሰፈላጊ ውዥንብር ይነዛል። የዛሬው ትውልድ በጊዜው አንዳንድ ስህተቶች መሰራታቸውን ቢያውቅም ፣ ድርጊቱን ግን በጊዜው ከነበረው የማቴሪያልና የዕውቀት ደረጃ ነጥሎ ለማየት በፍጹም አይገባውም። በዚያን ጊዜ የነበሩ መሪዎቻችን ከዚያ ውጭ ሊያስቡና ሊያደርጉ በፍጹም አይችሉም። እንደዚህ ማድረግ አልነበረባቸውም የምንል ከሆነ ፣ እኛ በዚያን ጊዜ በነሱ ቦታ ብንሆን ኖሮ የምንከተለው ፖለቲካ የተለየና የሰለጠነ ይሆናል ብሎ እንደማውራት ነው። ሺለር የሚባለው ታላቅ የድራማ ፣ የታሪክና የፍልስፋና ሰው ፣ አንድ ህብረተሰብ ራሱን በራሱ እስከሚያገኝ ደረስ ብዙ ውጣ ውረዶች እንዳሳለፈና ማሳለፈም እንዳለበት ያስገነዛባል። ስለዚህም የዛሬው ትውልድ በአፄ ቴዎድሮስና በአፄ ምኒልክ ቦታ ቢሆን ኑሮ ከነሱ የተለየ ፖለቲካ በፍጹም ሊያካሂድ አይችልም። እንዲያውም በድፍረት ልናገርና ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የተገለጠላቸውና ተራማጅ እንዲሁም ብልህ መሪ አፄ ምኒልክ ብቻ ነበሩ። አፄ ምኒልክ በስልጣኔው ገፍተው መሄድ ያልቻሉት ፣ አንደኛ የሳቸው አሰተሳሰብ ልክ እንደ አፄ ቴዎድሮስ በአካባቢው ከነበሩት አጃቢዎቻቸው በጣም ቀድሞ የሄደ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ ፣ በተለይም በአፄ ምኒልክ ዘመን የተለያዩ ኢምፐሪያሊሰት አገሮች አፈሪካን ለመቀራመት የተነሱበት ወቅትና ፣ በአገዛዙ ዙሪያም የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ በመከተል አገዛዙን ለማዳከምና ለማሳሳት ትግል ያደርጉ የነበረበት ዘመን ነበር። ከዚህ በተረፈ በጠቀላላው በአገሪቱ ውስጥ ህዝቡን እንደ አንድ ህብረተሰብ ሊያስተሳሰር የሚችል የማቴሪያልና የመንፈስ መሰረት አልነበረም። አፄ ምኒልክ የገጠማቸው ችግርና የተሰሸከሙት የታሪክ ኃላፊነት በጣም ከበድ ነበር ማለት ነው። ከሞላ ጎደል ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ፣ ከዚያ በኋላ የተፈጠረውን የዕደገትና የፀረ-ዕደገት ፈለግ መረዳት የምንችለው በዓለም አቀፍ ደረጃ የካፒታሊዝምን መስፋፋትና በየአገሩ አዳዲስ ኃይሎችን በመፍጠር ያልተስተካከለ ዕድገት እንዲፈጠር ከማድረጉ ጋር ለማያያዝ የቻልን እንደሆን ብቻ ነው። ይህም ቢሆን በጊዜው የነበረውን ዕውቀትና ንቃተ-ህሊና ያካተተ መሆን አለበት። ባጭሩ ስለብሄረ-ሰብ ጭቆናና በደል በምንጽፍበት ወቅት ሌሎችን ለመሸንገልና ለማስደሰት በሚል

Generated by Foxit PDF Creator © Foxit Software
http://www.foxitsoftware.com For evaluation only.

ብቻ የምንጽፍና የምንናገር ከሆነ ፣ ራሳቸው ጭቁን የሚባሉትንና ታጋይ ነን የሚሉትንም አንጠቅምም። በተራ የታሪክ አጻጻፍም የኢትዮጵያን ህብረተሰብ አወቃቀር በፍጹም መረዳት አንችልም። ፐላቶንና ሺለርን እየደጋገምን ማንበብ አለብን።

ያም ሆነ ይህ ፣ የዛሬው ስለብሄረ-ሰቦች የሚጻፈው ጽሁፍና እነሱንም በቀላል የትግል ክልል ውስጥ እንዲሳተፉ የምናደርገው ጥረት የትም አያደርሰንም። እንዲያውም የስልጣኔውን መንገድ የሚያዘናጋና ሳይንስና ቴክኖሎጂን በመቀዳጀት የተረጋጋ ህብረተስብ እንዳንመሰርት የሚያደርገን የታሪክን ጎማ ወደ ኋላ እንደማሽከርከር የሚቆጠር ነው። የተማሩ ሰዎች ሚና መሆን ያለበት በሚችሉት ፊልድ ገፍተው በመሄድና በመመራምር ለህብረተስባቸው ከዚህ አስከፊ ኑሮ እንዲላቀቅ አስፈላጊውን አስተዋፅዖ ማድረግ ነው። የዛሬ ሁለት ሺህ አራት መቶ ዐመታት ገደማ ፐላቶ በብሄረ-ሰብ ጉያ ስር ታሽጎ የሚካሄድን ፖለቲካ አደገኛነቱንና የስልጣኔ ጠንቅነቱን አሳይቷል። እንደዚሁም ፣ ሌሲንግ የተባለው የጀርመኑ ታላቅ የድራማ ሰው ፣ „ናታን ጥበበኛው“ በሚለው ድራማው በተለያዩ ሃይማኖቶች መሀከል የተፈጠሩትንና የሚፈጠሩትን የአስተሳሰብ ግጭቶች ካለመግባባትና የራስን ሚና ካለማወቅ የሚፈጠር መሆኑን በማመልከት ፣ በመሰረቱ በተለያዩ ሃይማኖቶች መሀከል መበላለጥ እንደሌለ አመልክቷል። ስለሆነም ፣ አማራ ኦሮሞን ወይም ትግሬን ፣ ወይንም ሌላውን ብሄረ-ሰብ አይበልጥም። ኦሮሞውም ሆነ ትግሬው እንዲሁም ሌላው ብሄረሰብ ከአማራው አይበልጡም። ይሁንና ደግሞ ሁሉም የየራሱ ችሎታና አስተዋፅዖ ሊያደርግ ይችላል። ስለሆነም ወደ ኋላ ተመልሰን ጉዳጓድ እየቆፈርን እንደዚህ ተደረገን ነበር ፣ ብዙ ግፍ ተፈጽሞብን ነበር ፣ እያለን ከሳይንስና ከህብረተሰብ አወቃቀር ታሪክ ውጭ ማውራት አይገባንም። ፐላቶ እንዳለው የሰው ልጅ ችግር አሁንም ቢሆን የማሰብ ኃይል ወይም የዕወቀት ችግር ነው። ችግራችን ነገሮችን በጠባቡ መመልከትና በጥላቻ መንፈስ ተወጥረን ወደ ርስ በርስ ለመጠፋፋት ማምራታችን ነው። ችግሩ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ችግር አይደለም። ችግሩ ይህ ተማርኩኝ የሚለው የሚነዛው ከታሪክ ሂደት ጋር የማይጣጣም ውዥንብር ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ከኛ የሚፈልገው አጉል ንትርክ ሳይሆን ፣ ዕውነተኛ ሰላምን አምጡልኝ ነው። ሳይንስና ቴክኖሎጂን በመፍጠር ኑሮዬን አቃሉልኝ ነው። የስልጣኔ ባለቤት አድርጉኝ ነው የሚለው። ባጭሩ ለሁሉም የሚስማማ ፣ ሁሉም እንደ ወንድማማችና እህትማማች ተከባብሮ ሊኖር የሚችልባትን አገር መስርቱልኝ ነው የሚለው። አታውርዱኝ ነው የሚለው። የኢትዮጵያ ህዝብ መልዕክቱ ፣ ከአንድ ምንጭ የተቀዳህ መሆንህን በመገንዘብ ፣ አማራ ፣ ትግሬ ፣ ኦሮሞና ኩሎ-ኮንታ... ወዘተ. እያልክ አታናቁረኝ ነው የሚለው። የማትችል ከሆነ በሰደት ዓለም ኑሮህን ግፋበት ነው የሚለው። ከዚህ ሌላ የሚለው ነገር የለውም። መልካም ንባብ!

ፈቃዱ በቀለ

fekadubekele@gmx.de

## ጠቃሚና መነበብ ያለባቸው መጻህፍት ፣

Chytry, Josef, The Aesthetic State, Los Angeles & London, 1989

Dawson, Christopher, Dynamics of World History, London, 1957

Seung, T.K, Kant`s Platonic Revolution in Moral & Political Phislosophy, Baltimore & London, 1994